ኢትዮጵያ፤ "አፍሪካዊቷ ቻይና"

ስሜነህ

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ በታህሳስ ወር መጀመሪያአካባቢ ከቻይናው ማዕከላዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ ሲ.ሲ.ቲቪ ጋር ቆይታ አድርገው ነበር ። የቆይታቸውም ጭብጥ የአገራችንን ኢኮኖሚ የተመለከተ ነው ። አገሪቷ ባለፈው ዓመት ከባድ የድርቅ አደጋ አጋጥሟት እንደነበረ በዚህ ቆይታቸው ያስታወሱት ጠቅላይ ሚንስትሩ፤ በዚህ ሳቢያ ከ8-10 የነበረው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ወደ 2 ነጥብ 9 ዝቅ ብሎ ማለቱን ገልጸዋል።

ሆኖም፤ በዚህ ዓመት በተደረገው የጋራ ጥረትና ርብርብ የግብርናው ዘርፍ የተሻለ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የሚጠበቅ መሆኑን፤ በአገልግሎት ዘርፍም አዎንታዊ ዕድገት እየተመዘገበ እንደሚገኝና በተለይም በኤሌክትሪክ አገልግሎት አቅርቦት ረገድ ትልቅ አቅም እየተፈጠረ መሆኑን ጠቅላይ ሚንስትሩ ለሲ.ሲ.ቲቪ መናገራቸውን አይተናል፤ ሰምተናል።

"አሁን በትክክለኛው መንገድ ላይ እንገኛለን። በዚህ ዓመት ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት ይመዘገባል ብለን እንጠብቃለን" ያሉት ሃይለ ማርያም ደሳለኝ፤ መንግስት የአገሪቷን የኤሌክትሪክ ኃይል ፍላጎት ለማሟላት የታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጨምሮ አዲስ በተመረቀው የጊቤ 3 ኃይል ማመንጫና በሌሎችም ላይ በትኩረት እየሰራ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

አገሪቷ የምስራቅ አፍሪካ የኃይል ትስስር አባል በመሆኗ ማመንጫዎቹ የቀጣናውን ፍላጎት ለማሟላት የሚያግዙ ሲሆን፤ የኢትዮጵያ ምጣኔ ኃብት ባለፈው ዓመት ያጋጠመውን የድርቅ አደጋ ተቋቁሞ 8 በሙቶ ዕድገት ማስመዝገቡ ይታወቃል። በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን አገሪቷ ቢያንስ የ11 በሙቶ አማካይ ዓመታዊ ዕድገት ለማስመዝገብ ባቀደችባቸው አምስት ዓመታት ኢኮኖሚው በየዓመቱ በአማካይ በ10 ነጥብ 1 በሙቶ አድጓል። የተመዘገበው ፈጣን ዕድገት በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ ከሚገኙ ከሰሃራ በታች ከሚገኙ የአፍሪካ አገራት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀርም በእጥፍ ከፍ ያለ እንደሆነ ተነግሯል።

ይህ ባለ ሁለት አኃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት ለአርሶና አርብቶ አደሮች፣ የግሉ ዘርፍና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በፍጥነት ማደግ እንደሚቻል ያሳየ መሆኑን የሚገልጹት መረጃዎች በተመሳሳይ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ባለ ሁለት አሃዝ ዓመታዊ ዕድገቱን በማስቀጠል ኢኮኖሚውን በአማካይ በ11 በሙቶ ለማሳደግ የሚያስችል አቅም መፈጠሩንም ያረጋግጣሉ ።

የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ለማስቻል እንደሚሰራ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሰነድ ላይ ሰፍሯል። የዚህ ተረክ አብይ ጉዳይም አንድ አመት ከመንፈቅ ያገባደደው የሁለተኛው ዙር እቅድ ዘመን በሰነዱ በተመለከተው ልክ የሚፈጸም መሆኑን አመላካች የሆኑ አስረጂዎችና በተለይም የውጭ ኢንቨስትመንት ዘርፍን የሚያሄስ ይሆናል።

በእቅዱ ሰነድ የተመለከተው ሁሉ እጅግ ከፍተኛ በሚባል ደረጃ የሚፈጸም እና በዚህም አገራችን ካሰበችው ከፍታ ላይ መድረሷ የማያጠራጥር ለመሆኑ በመጀመሪያ አስረጂነት የምጠቅሰው "ኢትዮጵያ በሥራዎችዋ የአፍሪካ ቻይና ለመሆን የያዘችው ትልም እውን እየሆነ ነው ሲል" የዘገበውን እና ለተረኬም በርእስነት ለተመረጠው ሃሳብ መነሻ የሆነኝን የዩናይትድፊድ ዎርድ ፕሬስ የተባለውን ድረ ገጽ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት እ.ኤ.አ በ1991 ወደ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት ከቻይና ጋር የነበረው ግንኙነት ዝቅተኛ ነበር፡፡ ነገር ግን ቀስ በቀስ የመሰረቱት በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አብሮነት ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ከፍተኛ እመርታ አሳይቷል፡፡ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረትን ጨምሮ የብዙ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ናት፡፡ ቻይናም አገሪቱ የፈጠረችውን ሐያልነትና የገበያ አቅም ከግምት ውስጥ በመከተት አጋርነቷን እያሳደገች ነው፡፡

በኢትዮጵያ ለሚታየው የመሰረተ ልማት ግንባታ ቻይና ከፍተኛ ብድርና ድጋፍ እንድታቀርብ አግዟታል፤ የሚለው ዩናይትድፊድ ዎርድ ፕሬስ ኢትዮጵያ ያላትን የህዝብ ብዛት መሰረት አድርጋ የሸቀጥ ፍላጎቷ እያደገ መጥቷል፡፡ ቻይና የአገሪቱ ከፍተኛ የንግድ አጋር ስትሆን የንግድ ልውውጥ ምጣኔው ከ3 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ማለቱንም ጠቅሷል፡፡

ኢትዮጵያ ከቻይና በምታገኘው ብድር በመታገዝ እድገቷን እያፋጠነች ትገኛለች፡፡ ለምሳሌ፤- የተከዜ ግድብ የሐይል ማመንጫ የተሰራው በቻይናውያን እገዛ ነው፡፡ በተጨማሪም ቻይና በአሞ ወንዝ ላይ የተገነባውን የሐይል ማመንጫ በመደገፍ ረገድም እንደዚሁ ሚና አላት፡፡ በኢትዮጵያ ከተገነቡት ግዙፍ የመንገድ አውታሮች አብዛኛዎቹ በቻይና ድጋፍ የተሰሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል የኢትዮ ጅቡቲ የባቡር መስመር ተጠቃሽ ነው፡፡ የቴሌኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት፤ የአዲስ አበባ የቀላል ባቡር ፕሮጀክት በቻይና ድጋፍ የተሰራ ነው፡፡

የሔሪቴጅ ፋውንዴሽንና የአሜሪካ ኢንስቲቲዩት ባወጡት ሪፖርት እ.ኤ.አ በ 2016 በኢትዮጵያ የነበረውን የቻይና ኢንቨስትመንት 20 ቢሊዮን ዶላር አድርሰውታል፡፡ የኢትዮጵያና የቻይና የኢኮኖሚ ግንኙነት እኤአ ከ2000 አንስቶ በቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትና በንግድ እየተጠናከረ ነው፡፡ በመንገድ ግንባታ፤ በኤሌክትሪክ፤ በቴሌኮሚኒኬሽን ዘርፍ ያለው የቻይና ተሳትፎ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከፍተኛ እመርታ አሳይቷል፡፡ በኢትዮጵያ እየተገነቡ ካሉት የመንገድ አውታሮች 70 በመቶ የሚጠጋው በቻይናውያን የሚገነባ ነው፡፡

የአፍሪካ የቀላል ማምረቻ ዘርፍ መዳረሻ ለመሆን ተስፋ ሰንቃ እየገሰገሰች ያለችው ኢትዮጵያ በመጪዎቹ ጥቂት ዓመታት ስድስት የኢንዱስትሪ ፓርክ የመገንባት ትልም ይዛለች፡፡ ይህ ትልም በቻይናና በእስያ የልማት ባንክ እንደሚደገፍ ድረ ገፁ ጽፏል፡፡ እያንዳንዱ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለግንባታ 500 ሚሊዮን ዶላር አካባቢ ይፈጃል፡፡ ይህ ደግሞ በእርግጥም ከኤዢያ አልፎ የዓለምን ኢኮኖሚ እየተቆጣጠረ በሚገኘው የቻይና ኢኮኖሚ ልክ የኢትዮጵያም ኢኮኖሚ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ማእከል ወደሚሆንበት አቅጣጫ እየተንደረደረ መሆኑን የሚያመላክት፤ ይልቁንም የሁለተኛው ዙር እቅድ ያለአንዳች መንገራገጭ በሰነዱ በተመለከተው ልክ የሚፈጸም እንደሆነ የሚያረጋግጥ ነው።

አገራችን አፍሪካዊቷ ቻይና ወደመሆን አቅጣጫ እያመራች ለመሆኑ ማሳያው ከላይ የተመለከተው ከቻይና ጋር ያላት ኢኮኖሚያዊ የሁለትዮሽ ስምምነት ብቻ ሳይሆን ከአውሮፓ ጀምሮ የአሜሪካና የመካከለኛው ምስራቅ አገራትና ባለሃብቶች ሁሉ ፊታቸውን ወደኢትዮጵያ ያዞሩበት እውነታም መኖሩ ነው።

ሳዑዲ አረቢያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በነዳጅ ምርታቸው በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት አገሮች አንዷ ነች። በአሁኑ ወቅትም በነዳጅ ላይ የተመሰረተውን ኢኮኖሚዋን በሌሎች አማራጮች ለመደገፍ የተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በማማረጥ ላይ ትገኛለች።

በርሃማዋ ሳዑዲ 30 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ አላት። ከእነዚህ መካከል 10 ሚሊዮኑ በልዩ ልዩ መንገዶች ወደ አገሪቷ የገቡ የውጪ ዜጎች ሲሆኑ፤ አንድ ሚሊዮኑ ደግሞ ኢትዮጵያዊያን ስለመሆናቸው ጥናቶች ያመለክታሉ።

ሳዑዲ አረቢያ ከኢትዮጵያ ጋር ረጅም ዘመን ያስቆጠረ ታሪካዊ ግንኙነትና የህዝብ ለህዝብ ትስስር አላት። ኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹን የእስልምና እምነት ተከታዮች ተቀብላ ማስተናገዷ ደግሞ የግንኙነታቸው ቀዳሚ ምዕራፍ ነው። ሁለቱ አገሮች ይፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የጀመሩት እኤአ በ1948 ቢሆንም፤ እስከ ደርግ ዘመነ-መንግስት መጨረሻ ድረስ ግንኙነቱ ጠንካራ መሰረት ሳይኖረው ቆይቷል።

ከዚያን ጊዜ ወዲህ የአገሮቹ ግንኙነት እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን፤ በተለያዩ ጊዜያት በመሪዎችና በከፍተኛ ባለስልጣናት ደረጃ በሁለቱም ወገን ግንኙነቱን ያሳድጋሉ የተባሉ ጉብኝቶች ተካሂደዋል። በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ታላቁ መሪ መለስ ዜናዊ፤ አሁንም በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ እና በሌሎችም የኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለስልጣናት በተለያዩ ጊዜያት በሳዑዲ አረቢያ የተደረጉ ጉብኝቶች የሚጠቀሱ ናቸው።

ጉብኝቶቹ የአገሮቹን የትብብር መስክ ወደ ኢኮኖሚ ትስስር ለመቀየር አስተዋጽኦ ማበርከታቸው ይታወቃል ። የሳዑዲ አረቢያ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ የንግድና ኢንቨስትመንት ተሳትፎ ለማደረግ ፍላጎት እንዲያሳዩና በሁለቱ አገሮች መካከል የትብብር ስምምነቶች እንዲፈረሙ መነሻ ሆነዋል።

ቀደም ሲል የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱን ለማጠናከርም የሁለቱ አገሮች ፓርላማዎች የወዳጅነት ማህበር መመስረታቸው ይታወቃል። ከዚህ ባሻገር በሁለቱ አገሮች መካከል በፖለቲካ፤ በከፍተኛ ትምህርት፤ በባህልና ቱሪዝም፤ በእርሻ እና በሌሎችም መስኮች የሁለትዮሽ የትብብር ስምምነቶች ተፈርመዋል። ሌሎችም በሂደት ላይ ይገኛሉ።

በቅርቡም በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የተመራ የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ሪያድ በማቅናት ከአገሪቱ ንጉስ፤ ከአልጋ ወራሹና ከሌሎችም ባለስልጣናት ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መክሯል። የሁለቱ መንግስታት ውይይት በፖለቲካ፤ በኢኮኖሚ፤ በጸጥታና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ በርዕሰ-ጉዳዮቹ ላይም መግባባት ላይ ተደርሷል። ከእነዚህ ስምምነቶች ታዲያ የሁለቱን አገሮች ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ወደ ጠንካራ የንግድና ኢንቨስትመንት ትስስር ማሳደግን የተመለከተው ስለአጀንዳችን እና ስለአፍሪካዊቷ ቻይና አይቀሬነት በአስረጂነት ሊጠቀስ የሚገባው ነው ።

በተለይም በንግድና ኢንቨስትመንት የሳኡዲ ባለሃብቶች በስፋት በኢትዮጵያ እንዲሳተፉና በግብርናው መስክ በሰብል፤ በእንስሳት እርባታ፤ በቆዳና ሌጦ እና በሌሎችም እንዲሰማሩ በጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የቀረበው ጥሪ ያለአንዳች ማቅማማት አወንታዊ ምላሽ ማግኘቱ አንደኛው እና ዋነኛው አስረጅ ነው።

በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማበረታታት እንደ አውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር በ2013 የተደራራቢ ቀረጥ ማስወገጃ ስምምነት መፈረሙ ይታወሳል። ይህም አሁን መንግስት ላደረገው ጥሪ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መሰረት መኖሩን ያመላክታል።

ኢትዮጵያ ቡና፤ ስጋ፤ ጥራጥሬ፤ የቅባት እህል፤ ሙዝና የመሳሰሉትን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ስትልክ፤ የተለያዩ ማሽኖችና ነዳጅ ደግሞ ወደአገር ውስጥ ታስገባለች። ይሁንና የንግድ ሚዛኑ እስካሁን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ያመዘነ ሲሆን፤ ይህ ስምምነት ሚዛኑን የሚያስተካክልና እጥፍ

ድርብ ጠቀሜታ የሚኖረው በመሆኑ ኢኮኖሚያችንን የተረጋጋና አንድ ደረጃ ከፍ የሚያደርገው እንደሚሆን የኢኮኖሚ ልሂቃን ይመሰክራሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሳዑዲ ዓረቢያ ባለሃብቶች በኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ለመሰማራት ከፍተኛ ፍላጎት በማሳየት ላይ ይገኛሉ። የአገሪቷ መንግስትም ዜጎቹ በውጭ አገሮች ሃብታቸውን ስራ ላይ እንዲያውሉ ከሚፈልግባቸውና ድጋፉን ከሚሰጣቸው አገሮች መካከል ኢትዮጵያ ከቀዳሚዎቹ ተርታ ተቀምጣለች።

እስካለፈው የፈረንጆች ዓመት መጀመሪያ ድረስ ሳዑዲ አረቢያ በኢትዮጵያ ያደረገችው የኢንቨስትመንት መጠን ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ነው። ይህ ስምምነት ደግሞ አገሮቹ ካላቸው ትስስርና ከፍላጎቱ አኳያ የንግድና የኢንቨስትመንት ግንኙነቱ ብዙ ርቀት መሄድ የሚያስችላቸው መሆኑን በመጥቀስ ነው ጠበብቶቹ ትርፋችንን ያሰሉት፤

በኢትዮጵያ ያለው ሰፊ የሥራተኛ አቅምና መሬት፤ እንዲሁም ውሃ  እና አስተማማኝ የሃይል አቅርቦት ይልቁንም አስተማማኝ ሰላም የማረከውና እጅ ያሰጠው ሳኡዲን ብቻ አይደለም። ከወደ አውሮፓ ሄደን ሰሞንኛ የሆነችውን ቱርክ መጥቀስ ይቻላል። ቱርካውያን ባለሃብቶች ከዚህ ቀደም ከነበረው በእጥፍ ለእርሻና ኢንዱስትሪ አመቺ የሆነችው ኢትዮጵያ  የአፍሪካ በር መሆኗን በመመስከር ፊታቸውን ወደአገራችን እያዞሩ ነው። ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል ።እነዚህ አገራት ሲመጡ አገራችን በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያላትን ታላቅ ቦታም ተረድተው እንደሆነ እራሳቸው ሰርክ የሚናገሩት ነው ።

ለውጭ ኢንቨስትመንታችን ፍሰት አስተማማኝ መሆንና በማያባራ ደረጃ ላይ መድረስ አስተዋጽኦ ካደረጉት እና ስለአፍሪካዊቷ ቻይና ሊጠቀሱ ከሚገባቸው ዘርፎች መካከል ሌላው የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ነው ።

በአፍሪካ ዘመናዊ የሆነው የኤሌክትሪክ ባቡር ኢትዮጵያን ከጅቡቲ እንደሚያገናኝ የጻፈው ኢንተርናሽናል ሪሌሺን ፐብሊሺንግ የተባለ ድረ ገጽ፤ ከኢትዮጵያ የወጪና ገቢ ንግድ 95 በመቶ የሚሆነው የሚጓጓዘው በዚሁ መንገድ እንደሆነ ይጠቅሳል። ለብዙ ዓመታት የሚያገለግለውና ብዙ ቢሊዮን ዶላር የወጣበት ፕሮጀክት 752 ነጥብ 7 ኪሎ ሜትር የሚረዝም ሲሆን፤ በሰአት 120 ኪሎ ሜትር የሚበርረው ባቡር በመኪና ይፈጅ የነበረውን የሶስት ቀን መንገድ ወደ አስራ ሁለት ሰአት በማሳጠር በወጪ ንግድ እንቅስቃሴያችን ላይ የሚኖረውን ከፍተኛ ሚና ያረጋግጣል፡፡

በኢትዮጵያ የተገነባው አዲሱ የባቡር መስመር የምስራቅ አፍሪካን ኢኮኖሚ በማሳደግና በማስተሳሰር በኩል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ድረ ገጹ ፅፏል፡፡ ይህ ደግሞ በእርግጥም አገራችን አፍሪካዊቷ ቻይና ወደመሆን አቅጣጫ በማምራት ላይ መሆኗን የሚያመላክት ነው፡፡

አዲሱ የባቡር መስመር የአገሪቱን ኢኮኖሚ ሽግግር በማፋጠን በኩል ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ ግንባታው በኢትዮጵያ፤ በመካከለኛው ምስራቅ፤ በአውሮፓና በመካከለኛው እስያ አገራት  መካከል ያለውን የንግድ ልውውጥ ከማሳደጉ በላይ ጅቡቲን ከሚያድገው የንግድ ትስስር ተጠቃሚ ያደርጋታል፡፡ የመካከለኛው ምስራቅ አገራት ወደ አፍሪካ ለመግባት ጅቡቲን ቀዳሚ ምርጫቸው በማድረግ በቀጠናው ያላትን ተፈላጊነትና የንግድ መዳረሻነት ከፍ ያደርጉላታል፡፡ አሁን ላይ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን የአትክልት፤ የፍራፍሬና የአበባ ንግዱን ወደ መካከለኛው ምስራቅ በመላክ ተጠቃሚ ለመሆን የባቡር መስመሩ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡

ፊታቸውን ወደ አፍሪካዊቷ ቻይና በማዞር ላይ የሚገኙት አውሮፓውያን አሜሪካና የመካከለኛው ምስራቅ አገራት ብቻ አይደሉም፤ አፍሪካውያንም ናቸው።የነናይጄሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ሞሮኮን በመከተል አልጄሪያም  ወደአፍሪካዊቷ ቻይና ከሰሞኑ እጆቿን ዘርግታለች። አልጄሪያውያን ባለኃብቶች በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ ተጠቅመው ኃብታቸውን ማፍሰስ እንደሚፈልጉ በአልጄሪያ ኦራን ከተማ በተካሄደ የቢዝነስ ፎረም ላይ ገልጸዋል። በዚሁ ጊዜ የኦራን ከተማ የንግድ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሞአድ አቢድ በመጪው የካቲት የአልጄሪያ የንግድ ምክር ቤት አንድ ልዑክ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ ተናግረዋል።

ልዑኩ ከኢትዮጵያውያን ባለኃብቶች ጋር በመወያየት በመረጡት የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ሲሉ መናገራቸው አገራችን በእርግጥም አፍሪካዊቷ ቻይና ወደመሆን እያመራች መሆኑን እግረ መንገዱን የሚያመላከት ነው።